# የደቂቀ እስጢፋኖስ ዐውደ ንባባዊ ትንታኔ

ፍሬህይወት ባዩ[1]

**አኅጽሮተ ጽሑፍ**

የዚህ ጥናት ትኩረት ገድል ሲሆን ደቂቀ እስጢፋኖስ ("በህግ አምላክ") በሚል ርእስ አራት ገድሎችን በአንድ ጥራዝ የያዘ መጽሀፍ ነው። መጽሀፉ በጌታቸው ሀይሌ ከግዕዝ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ ለሁለተኛ ጊዜ በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ፕሬስ የታተመ ነው። የጽሁፉ ዋና አላማ የገድልን ጽንሰ ሀሳብ መሠረት በማድረግየደቂቀ እስጢፋኖስን ገድል በዐውደ ንባባዊ ስልት መተንተን ነው። ገድል የተጻፈላቸው በአንድ ገዳም የሚኖሩ መነኮሳት ሲሆኑ የተጋድሎ መነሻ ስለገዳማዊ አኗኗር የነበራቸው የአረዳድ ልዩነት ነው። በተለይም የተጋድሎው መሪ አባ እስጢፋኖስ ሲሆኑ እሳቸው ካለፉ በኋላ ተጋድሎው ከግለሰብ ወደ ተቋም አድጎ ተቋሙ ደቂቀ እስጢፋኖስ ተብሏል። ይህ ጥናት የአባ እስጢፋኖስና የተከታዮቻቸው ገድል ዋንኛው ማጠንጠኛ "ሀሳብን በሀሳብ እና ሀሳብን በስልጣን መርታት" የሚል አብይ ጭብጥ እንዳለው ያሳያል። የአባ እስጢፋኖስና የተከታዮቻቸው ገድሎች እንደሌሎች ገድሎች ዐውደ ንባቦቹ የሃይማኖት ናቸው። ሆኖም በአውደ ንባቦች ውስጥ ያሉት ድርጊቶች ሁነቶች በእምነት አይን አይተን በእምነት ጆሮ ሰምተን በእምነት ልቡና አምነን ይሁን ብለን የምናስተናግዳቸው ብቻ አይደሉም። የደቂቀ እስጢፋኖስ ገድል ከሌሎች መሰል ገድሎች ልዩ የሚያደርገው አንደኛው በተሳታፊ ተመልካች መጻፉ ሲሆን ሁለተኛው ከተለመደው በቅዱሳን እና በተቃራኒው ባለ ወገን መካከል የተደረገ መንፈሳዊ ውጊያ ሳይሆን በአንድ ሃይማኖት ተከታዮች መካከል የተፈጸመ መሆኑ ነው።

## 1. መግቢያ

የአባ እስጢፋኖስና የተከታዮቻቸው ገድል በተጻፈበት በ15 መ/ክ/ዘመን "ገድል" በአፍ ሙሉ ለግእዝ ስነ ጽሁፍ አዲስ ነው ባይባልም በሰፊው ይተረጎም፣ በሀገር በቀል ድርሰትነትም ይደረስ ነበር። ሌሎቹ ጸዋትው "ተአምር"፣ "ድርሳን"፣ "ውዳሴ"፣ "ቅዳሴ"፣ "መልክዕ"፣ "ስንክሳር" በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ "ሃይማኖታዊ" ከምንላቸው ውጭ "ዜና መዋዕል"፣ "ታሪክ ነገስት"፣ የፍልስፍና መጻህፍት "ታሪክ' (ለምሳሌ አባ ባሕርይ ስለ ኦሮሞ ህዝብና ስለሥርዓቱ የጻፉት)፣ "ሐተታ" (ለምሳሌ የዘርያእቆብ አክሱማዊ እና የወልደ ሕይወት እንፍራዛዊ ሐተታዎ፣"ሕግ" (ለምሳሌፍትሐ ነገስት፣ ዓምደ ጽዮን አጻፈው የሚባለው ሥርዓተ ህግ ወዘተ ናቸው) እንደ ቀደመው የአክሱም ዘመን በዚህኛውም ዘመን ሃይማኖቱ ፖለቲካው እና ሥነ ጽሁፉ የተቆራኙ በመሆናቸው ጽሁፎቹ ሲጠኑ ከሶስቱም አንጻር ይሆን ዘንድ የዘመኑ አውድ የግድ የሚል ይሆናል። ማለትም እዚህ ላይ ሃይማኖቱ፣ እዚያ ላይ ፖለቲካው፣ እዚህ ላይ ሥነጽሑፉ ብለን ለመለየትና ነጣጥለን ለማየት የጊዜው ማህበራዊ፣ ባህላዊ እና ርዕዮተ ዓለማዊ ሁኔታ አስቸጋሪ ያደርግብናል። ስለዚህ፣ ቅኚታችን (approach) ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሃይማኖታዊ/ፍልስፍናዊ (theological/philosophical)፣ ባህላዊ፣ ርእዮተ ዓለማዊ (ideological)፣ ምግባራዊም

[1] አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ፣ የስነጽሁፍና ፎክሎር ተመራማሪ

(ethical)፣ ሊሆን ይችላል። ኪነታዊ ከሁሉም ሊለቀም የሚችል ነው[2]። መረጃዎች ዘመን ተሻግረው ለትውልድ እንዲተላለፉ በጽሁፍ መስፈራቸው ያለው ጠቀሜታ በገድል ውስጥ "ከእናንተ በኋላ ለሚመጡ ምስክር እንዲሆን አይተውም እንዲደሰቱበትና እንደዚያ እንዲያደርጉ ከእናንተ በፊት ስለነበሩት ወንድሞቻችሁ ገድልና ጻማ[3] ሁሉ አሁን ጻፉ (ደቂቀ እስጢፋኖስ 265)። በማለት የጽሁፍ ጥበብ ምን ያህል የተለመደ እና የዳበረ እንደሆነ የመነኮሳቱን አርቆ አሳቢነት የሚጠቁም ነው። የገድሉ መጻፍ ዋና አላማ የገድሉ ባለቤት የሆኑ መነኮሳትንተጋድሎ ለመዘከር ነው።

በሀገራችን በተለይም አባ እስጢፋኖስና ተከታዮቻቸው በኖሩበት በ15ም.ክ.ዘ የነበረውን የጽሁፍ ጥበብ ስንመለከት፣ የጽሁፍ ቋንቋ ምን ያህል አድጎ እንደነበረ የሚያሳይ ነው። ደቂቀ እስጢፋኖስ በኢትዮጵያዊ ጸሀፊያን በግዕዝ ቋንቋ ከተጻፉ ገድላት ለየት ያለጠባይ አላቸው። ለምሳሌ፣ በአጻጻፍ ቴክኒክ፣ ድርጊቱ ተፈጽሞ ሳይረሳ በተሳታፊዎቹ (በባለቤቶቹ) እና በቅርብ ሰዎች መጻፉ፤ የገድሉ ተርጓሚ በመጽሀፉ መግቢያ እንዲሁም በግርጌ ማስታወሻ በሚሰጡት ማብራሪያ ደቂቀ እስጢፋኖስን ከሌሎች ገድሎች ለየት ያደርገዋል።

የዚህ ጥናት ትኩረት ደቂቀ እስጢፋኖስበአጠቃላይ በአራቱ ገድላት ላይ ያተኮረ ነው። እነዚህም ገድለ አባ እስጢፋኖስ፣ ገድለ አበው ወአኀው፣ ገድለ አባ አበከረዙን እና ገድለ አባ ዕዝራ ናቸው። በደቂቀ እስጢፋኖስ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡት ሶስት ገድሎች ለተጋድሏቸው መነሻ የአባ እስጢፋኖስ ፈለግ ነው። የጉንዳጉንዶ ገዳም የአባ እስጢፋኖስን ገድል[4] አሳትሟል። በተጨማሪም ደቂቀ እስጢፋኖሳዊያንን በተመለከተ ሌሎች ገድሎች እንዳሉ የሚጠቁሙ መረጃዎችም አሉ (በአማን 2009፡15)።

የጥናቱ ዋና አላማ በደቂቀ እስጢፋኖስ ገድል ላይ አውደ ንባባዊ ትንታኔ ማቅረብ ነው። የመጽሀፉን አብይ ትኩረት ከአውደ ንባቡ ለማውጣት በገድሉ ውስጥ የተጠቀሱ የተለያዩ ኮዶችን[5] በመምረጥ ተተንትኗል። ትንተናው ገድል የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ መነሻ ያደረገ ነው።

የጥናቱ ስልት ዐውደ ንባባዊ ትንተና (textual analysis) የተከተለ ነው። ተግባቦታዊ ሂደቱ የሚከናወንበት ጊዜ፣ ቦታ እና ተግባቦቱን ያመነጨው ዓቢይ ጉዳይ ዐውድ ይባላል (ብርሃኑ 1995፡6)፡፡ ዐውደ ንባብን ለዚህ ጥናት እንዲመች አጥብበን ስንመለከተው፣ ዐውደ ንባብ (context) የሚጠናው ቴክስት የቀረበበትን ዐውድ ለማሳየት ነው። ነገር ግን አንድ ቴክስት ሲጠና

---

[2]ዮናስ አድማሱ የክፍልውስጥ ዳረጎት (ማስታወሻ)፣ (2000ዓ.ም)።

[3]"ጻማ" ማለት "ድካም" ማለት ሲሆን መነኮሳት እግዚአብሄርን ለመለማመጥ ራሳቸውም ሆኑ ሌሎች የሚያመጡባቸው መማቀቅ ነው፤ ለጽድቅ ሲሉ ሰውነታቸው ድቅቅ እስኪልና እስኪደክም ድረስ ይጾማሉ፤ ለሃይማኖታቸው በእስር ቤት ይማቅቃሉ። የሰማይ ቤቱ ዋጋ በጻማው መጠን እንደሆነ ይታመንበታል። ጻማ "የድካም ፍሬ" ማለትም ይሆናል። "ጻማችንን ቀሙን" ማለት "ደክመን በላባችን ያገኘነውን ወሰዱብን" ማለት ነው (ደቂቀ እስጢፋኖስ 51)።

[4] ከገድለ አቡነ እስጢፋኖስ ዘጉንዳጉንዶ (ዘአጠሞ መምህር ወማህበር ዘጉንዳጉንዶ ደብረ ገሪዛን ማሪያም ገዳም፣ 1996።

[5]"the code" ለምናሄደው ትርጓሜ፣ ለምንዘረጋው የሀቲት ጉባኤ ቁልፍ ሀሳብ (ዮናስ አድማሱ የክፍል ውስጥ ዳረጎት [ማስታወሻ] 2000)።

ሌላ ቴክስት ስለሚያስፈልገው፣ የሚመጣው ቴክስት በዋናነት ለሚጠናው ቴክስት ማናበቢያ ስለሚሆን የዐውደ ንባቡን ትርጉም (inter textual) ይጨምራል። በዚህ ስልት ትንታኔው የዐውደ ንባቡ አካል ይሆናል። የገድሉ ዐውደ ንባብ በቀጥታ ቴክስትን የሚመለከት ነው። ከቴክስትም በጽሁፍ የቀረበ ገድል ላይ ብቻ ያተኩራል።

ገድል ውስጥ ያሉ የተለያዩ ኮዶችን መልካቸውን ትተን ጠባያቸውን ከተመለከትን፤ ድርጊቶችን ሁነቶችንና ሁኔታዎችን ሳይሆን የድርጊቶቹን የሁኔታዎቹን ውስጣዊ ባህሪያት ከመረመርን የገድሉን መነሻ እና መድረሻ እንለያለን።

**2. የጽንሰ ሀሳብ መነሻ**

**ገድል**፡-ትግል፣ ፈተና፣ ውጊያ፣ ሰልፍ፣ ድልና አክሊል እስኪገኝ ድረስ የሚደክሙት ድካም፣ የሚሰሩት ስራ፣ የሚቀበሉት መከራ፣ መንፈሳዊ ዜና ወግ ታሪክ የቅዱሳን መከራ ፀጋ ተጋድሏቸውን የሚናገር ጽሁፍ ነው (ኪዳነ ወልድ 1948፡ 301)።

ስለገድልነቱ "ገድለ" ብሎ የሚጀምረው የመጽሀፉ ርእስ አንዱ መረጃ ሲሆን ሁለተኛ ገድሉ የኢትዮጵያ ጸሀፊያን እንደ ደረሷቸው የተለመደ መግቢያ "በስመ አብ ወወልድወመንፈስ ቅዱስ" ይልና፣ "...የብፁዕና የቅዱስ፣ የሃይማኖት ዓምድ የክርስቲያን ሙብራት (የሰማእትነት) አክሊል የደፋ...የአባ እስጢፋኖስ ገድልና ሰማእትነትእነሆ (ደቂቀ እስጢፋኖስ 56)" በማለት ይጀምራል።

በገድል ብያኔ በተለይ ከአፈ-ታሪክ እና ከሚት ጥናት ጋር ተያይዞ የአባ እስጢፋኖስ ገድል አፈ-ታሪክ መሆን ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ የታሪክ አካል እንደሆነም ይጠቁሙናል። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ገድላት ካላቸው ጠቀሜታ አንዱ ታሪካዊ ዋጋቸው እንደሆነ ዋቢዎችን በመጥቀስ ጠቁመዋል (ዳንኤል 2011:68)።

አንድ ሃይማኖታዊ ተጋዳሊ አላማው የማይታየውና ተስፋ የሚያደርገው ዘላለማዊ ህይወት ነው። ከሞት በኋላ እደርስበታለሁ ብሎ ለሚያምነው ዘላለማዊ ህይወት ለመድረስ በአካልም በመንፈስም ከፍተኛ ተጋድሎ ያደርጋል። የአባ እስጢፋኖስ እና የተከታዮቻቸው ተጋድሎ ዘላለማዊ የሆነውን ህይወት ለመውረስ ነው።

ክሮው ፎርድ ደግሞ ገድልና ሚትን አቃይጦ ገድላዊ-ሚት ይለዋል። ቅዱሱ በእውን ኖሯል ብለን ካሰብን ገድላዊ ሚት ነው። ተራኪዎች ሚታዊ ጭብጦችን ይጨምራሉ (Crawford, 1961:6)። በማለት "በእውን ኖሯል ብለን ካሰብን" የሚለው አፈ-ታሪክንም እንደሚጨምር የሚጠቁም ነው። የዚህ ጽሁፍ ትኩረት የሆኑት ባለታሪኮችበእውን በዚህ ዓለም ነበሩ። ለዚህም ማሳያ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከንጉስ ዘርያዕቆብ ጋራ በነበረው የሃይማኖት ክርክር የሚታወቁና አስተምህሯቸውም ዘመን የተሻገረ እንደሆነ ተርጓሚው ጭምር በመቅድማቸው ሲጠቁሙ፤ "ከረጅሙ ታሪካችን ውስጥ ለዛሬ እነዚህን ገድሎች የመረጥኩት ደቂቀ እስጢፋኖስ ከእኛ ዘመን በፊት ለእምነታቸው ምሳሌ የሌለው ከፍተኛ ትግል ያሳዩ ሆነው ስላገኘኋቸው ነው።" ሲሉ በገድሉ ውስጥ ታሪካቸው የቀረበው ግለሰቦች በእውን በዚህ ዓለም ስለመኖራቸው ለሚነሳው

ጥያቄ ምላሽ የሚሰጥ ነው። ከኢትዮጵያ የታሪክ ምሁራን መካከል የደቂቀ እስጢፋኖስን ቀዳሚ ቃል የጻፉት[6] “ይህ ገድል በሚቀጥለው ንጉስ ዘመነ መንግስት (1468-1478እአአ) ነገሩ ተፈጽሞ ገና ሳይረሳ ከአጭር ጊዜ በኋላ ስለተጻፈ ተአማኒነቱ ከፍተኛ መሆኑን እርግጠኛ መሆን ይቻላል (ደቂቀ እስጢፋኖስ 16)።

በገድል ብያኔ በተለይ ከአፈታሪክ እና ከሚት ጥናት ጋር ተያይዞ የአባ እስጢፋኖስ በአንድ የታሪክ ዘመን በእውን ስለመኖራቸው ጥያቄ የማያስነሳ እንዲያውም ከሌሎቹ ገድሎች የበለጠ ተአማኒነት እንዳለው እና የገድሉ ታሪካዊ ማስረጃነት የማያጠያይቅ መሆኑን ያረጋግጣሉ።

አንድ ለተጋድሎ የሚነሳ ግለሰብ ይዞ የሚነሳው አላማና ለስኬቱ ሲል የሚያልፍባቸው አባጣ ጎባጣ መንገዶች አሉ። አላማው ፖለቲካ፣ ሃይማኖት ወይም ሰብአዊነት ሊሆን ይችላል። በገድሉ ውስጥ ያሉ ባለታሪኮች “ቅዱስ” ያስባላቸው ገድል ያስጻፈላቸው ለሚከተሉት ሃይማኖት ከእነርሱ የቀደሙ የሃይማኖቱ ተከታዮች ለደነገጉትና በጽሁፍ ላሰፈሩት ቀኖና ታማኝ መሆን ነው። ምድራዊው ተጋድሎ ከሞት በኋላ አለ ለሚሉት ዓለም ለመብቃት የሚደረግ ውጊያ ነው። ውጊያውን ማሸነፍ ከሞት በኋላ ባለው ዓለም በተድላ ዘላለማዊ መሆን ነው። አባ እስጢፋኖስም ሆኑ ተከታዮቻቸው ከሞት በኋላ አለ ብለው በሚያምኑት ዓለም በደስታ ለመኖር የከፈሉት ዋጋ ነው።

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን (የኢ.ኦ.ተ.ቤ) ደቂቀ እስጢፋኖስን ከቅዱሳኗ መካከል ባታሰፍራቸውም ገድሉን የጻፉትና ተከታዮቻቸው ቅዱስነታቸውን አምነው ገድል ጽፈውላቸዋል። ስለዚህ በገድሉ ጸሀፊዎች እምነትና አቋም መሠረት ከላይ የተቀመጠውን የገድል ብያኔ[7] ተከትለን መጽሀፉን እንመረምራለን። አንድ ለሃይማኖታዊ አላማ የሚጋደል ግለሰብየማይታየውና ተስፋ የሚያደርገው ዘላለማዊ ህይወት ነው። ከሞት በኋላ ወደሚደርስበት ዘላለማዊ ህይወት ለመድረስ በአካልም በመንፈስም ከፍተኛ ተጋድሎያደርጋል።

[6] ሽፈራሁ በቀለ (ፕሮፌሰር)።

[7]በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ቀኖና መሠረት ይሄንን ምድራዊ ተጋድሎ በአግባቡ ተወጥቷል በማለት ቅዱስ ተብሎ ገድሉ ይጻፋል። ሆኖም የአባ እስጢፋኖስን ገድል ለየት የሚያደርገው ስለ አባ እስጢፋኖስ ቅድስና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሃይማኖት ተከታዮች መካከል ያለው የተለያየ አቋም ነው። አንደኛው አቋም አባ እስጢፋኖስ ‘ቅዱስ አይደሉም፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አታውቃቸውም እንዲያውም ተወግዘዋል የሚል ነው። ውግዘታቸውን በተመለከተም የደቂቀ እስጢፋኖስ ተርጓሚም፤ “ታሪካቸውን እዚህ የማቀርበው አባ እስጢፋኖስና ተከታዮቻቸው (ደቂቀ እስጢፋኖስ) የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የማትቀበላቸው እንዲያውም የተወገዙ አድርጋ የምታያቸው… ናቸው።” በማለት በመጽሀፉ መቅድም ጠቁመዋል። ሁለተኛው አቋም ገድሉን የጻፉት እና ተከታዮቻቸው አባ እስጢፋኖስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታይ ነበሩ። አባ እስጢፋኖስና ፈለጋቸውን የተከተሉ መነኮሳት አባ እጢፋኖስ ይኖሩበት የነበረው ገዳም የነበሩ መነኮሳት ጭምር የሃይማኖት ህጸጽ የለብንም ብለው ያምናሉ። ስለዚህ አባ እስጢፋኖስንም ሆነ ተከታዮቻቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሃይማኖት ተከታዮች እንዲያውም በዘመኑ ከነበሩት ሌሎች መነኮሳት በተለይም የንጉስ አጼ ዘርአያእቆብ ተከታይ መነኮሳት የተሻሉ እና ለቅድስና የበቁ ናቸው። የሚል አቋም እንዳላቸው ገድሎቹ ይነግሩናል። የኢ.ኦ.ተ.ቤ የደቂቀ እስጢፋኖስን ገድል መቀበል አለመቀበል የዚህ ጥናት ጉዳይ ስላልሆነ ከዚህ በላይ ማለቱ ከጥናቱ አላማ አኳያ ተገቢ አይደለም።

አንድ ለሃይማኖታዊ እምነቱ የሚጋደልግለሰብ አላማው የማይታየውንና ተስፋ የሚያደርገውን ዘላለማዊህይወትበተድላ ለመኖር ነው። የዚህ አይነቱ ባለገድል ከሞት በኋላ ወደሚደርስበት ዘላለማዊ ህይወት ለመድረስ በአካልም በመንፈስም ከፍተኛ ተጋድሎ ያደርጋል። የአባ እስጢፋኖስ ተጋድሎም ይሄው ነው።

### 3. ገድለ ደቂቀ እስጢፋኖስአውደ ንባባዊ ትንታኔ

ገድለ ደቂቀ እስጢፋኖስ አጠቃላይ አውድ የሚያተኩረው በአባ እስጢፋኖስ ፈለግ ላይ ነው። የገድሉ ባለቤት የሆኑት አባ እስጢፋኖስ የኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታይ ናቸው። ስለ ሃይማኖታቸው በተለይም መነኩሴ እንዴት መኖር እንዳለበት የተጻፉ መጻህፍትን በመመርመር መጻህፍቱ በሚያዙት መሠረት ይኖራሉ እንጂ የመነኮሳቱን የልማድ አኗኗር አይከተሉም። አባ እስጢፋኖስ መጻህፍቱ ከሚሉት ውጭ ከሌሎች መነኮሳት ጋራ በማንኛውም ጉዳይ ማውራት አይፈልጉም። ከቻሉ አለማድመጥን፤ ከሰሙም ዝምታን ይመርጣሉ። በጥቅሉ አባእስጢፋኖስ ጥብቅ የሆነ ክርስቲያናዊ ስነምግባርን ይከተላሉ። የብህትውና ኑሮም ጥብቅና መጽሀፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለው መሆን ይገባዋል ባይ ናቸው። የመነኮሳቱ ልማድ በአባ እስጢፋኖስ ዘንድ ቦታ ስላልነበረው ቅሬታ የነበራቸው መነኮሳት ቅሬታቸውን በቅኔ (በአሽሙር) መልክ "የደብሩ ልማድ ያልሆነ የሚያደርግ" (ደቂቀ እስጢፋኖስ 232) ሲሉ ተቀኙ። የአባ እስጢፋኖስ የደብሩን ነዋሪዎች ልማድ ያለመቀበል እና በመጽሀፍት መመሪያ "ብቻ" መኖር ከቅሬታም አልፎ ለአደባባይ ክስ አበቃቸው።

አባ እስጢፋኖስ ይኖሩበት በነበረው ገዳም ከሚኖሩት ጥቂቶቹ "በሃይማኖት መጽሀፍት ቀኖና ብቻ አይኖርም፤ የተለመደው የቀደሙት ገዳማዊያን አኗኗርም ያስፈልጋል።" ሲሉ እንደ አባ እስጢፋኖስ ያሉት ደግሞ "በልማድ መኖር አያስፈልግም" በማለት የሃሳብ ልዩነት ተፈጠረ። ይህ ሁለት ወገን የሆኑበት የህሳብ ልዩነት ሰፍቶ የአንድ ሃይማኖት ተከታይ መነኮሳት ከሳሽና ተከሳሽሆኑ። የእነዚህ ሁለት ወገኖች የሀሳብ ልዩነት ምክንያት እና ውጤቱን ከአባ እስጢፋኖስ ገድል ከዐውደ ንባቡ መካከል ጥቂት ኮዶችን ወስደን እንደሚከተለው እንመለከታለን።

### 3.1 ሁሉ አድርገውታል በማለት የነገር ድካም?[8]

አባ እሰጢፋኖስ ፤ መነኮሳቱ የሚከተሉት ሃይማኖት አንድ ሆኖ፣ በየገዳማቱ ያሉ መጻህፍት ተመሳሳይ ሆነው፣ ከሳሽና ተከሳሽ ለምን ኖረ? ልዩነቱ የአረዳድ ከሆነ ለምን የትኛው ትክክል እንደሆነ የሚለይበት መድረክ አይኖርም? የሚል ጥያቄ ይጠይቁ ነበር። በወቅቱ ስለሃይማኖት መጻህፍት በብዛት መኖር እንዲሁም ማንበቡ ብቻ በቂ እንዳልሆነና በንባባቸው ላይ ስለአረዳዳቸው ውይይት ቢኖር የሚል ምኞትም ጭምር እንደነበራቸው ጥቆማ ይሰጡናል። ይሄውም፤ መጻህፍት በሀገራችን በየቤተክርስቲያኑ ሞልተዋል። ሁሉም እውነትን በማስተማር ከብሉይ እስከ ሐዲስ እየተባበሩ ሳለ፣ በቃላቸው አፈራረድ የሚረዳ ይግባኝ የሚባልበት የፍርድ

---

[8] ደቂቀ እስጢፋኖስ (109)

አደባባይ የለም፤ ሁሉም አቋሙ በፈቀደለት ይሄዳል (ደቂቀ እስጢፋኖስ 71)። በማለት የተፈጠረውን የሀሳብ ልዩነት እንዲጠብ ይፈልጉ ነበር።

የገድሉ ተርጓሚቀደም ባለ ስራቸው በእነደቂቀ እስጢፋኖስ ዘመንየነበረውን የገዳማት የእውቀት ሽግግር ሲገልጹ፦"ደቂቀ እስጢፋኖስ ወደ መድረክ ከመውጣታቸው በፊት ገዳማት የራሳቸው የአገልግሎት መጻህፍት እንዲደርሱ የየራሳቸውን ደንብ እንዲዘረጉ (እንዲያወጡ) የኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖትን በራሳቸው እውቀት ልክና በመረዳታቸው መጠን እንዲተረጉሙ ሙሉ ነጻነት ነበራቸው (Getachew, 1983: 110)።

አባ እስጢፋኖስም መጻህፍቱን በተረዱት ልክ በተግባር መኖር መፈለጋቸው ልማዳዊውን አኗኗር ከሚከተሉ ገዳማዊያን ጋር አጋጫቸው።አባ እስጢፋኖስ በገዳሙ ያልተለመደ አኗኗራቸው ከሌሎች መነኮሳት እና የገዳሙ አገልጋዮች ዘንድ ቅሬታ ማሳደሩ ጥያቄ ፈጠረባቸው። አባ እስጢፋኖስ ለጥያቄያቸውምላሽ እንዲያገኙ በወቅቱ የነበሩት ጳጳስ[9]ጠየቁ። ጳጳሱም አባ እስጢፋኖስ ልክ መሆናቸውን ከማረጋገጥም በላይሌሎች መነኮሳት ፈለጋቸውን እንዲከተሉ ፈቀዱላቸው። እንዲያውም አባ እስጢፋኖስ በየገዳማቱ እየዞሩ እንዲያስተምሩ ጭምር ፈቃድ ሰጧቸው። ሆኖም አባ እስጢፋኖስ ዞሮ በማስተማሩ አልተስማሙም። የጳጳሱ የአባ እስጢፋኖስን ሀሳብ ትክክል መሆን መደገፋቸው ለአባ እስጢፋኖስና ለተከታዮቻቸው በአቋማቸው እንዲጸኑ ብርታት ሆኗቸዋል።

የአባ እስጢፋኖስ አቋም ተጋሪዎች ቁጥር መብዛትና በተግባርም ያመኑበትን ለመኖር መጠንከር ሀሳባቸውን በመቃወም ቀድሞ ይኖሩበት ከነበረ ገዳም ላባረሯቸው መነኮሳት ስጋት ሆነባቸው። የአባ እስጢፋኖስና የተከታዮቻቸው ተቃዋሚዎችየተጸጸቱ በመምሰል አባእስጢፋኖስን በማግባባት ወደ ገዳማቸው እንዲመለሱ በማድረግ ቅጣት ጣሉባቸው። ቅጣቱም የአባ እስጢፋኖስን እጅና እግርበእግር ብረት በማሰርሁለት ወር በጨለማቤት ማቆየት ነበር።አበምኔቱ በድርጊታቸው ተፀፅተው አባ እስጢፋኖስን ስላደረሱባቸው መከራ ይቅርታ ጠይቀው ወደፈለጉበት እንዲሄዱ ፈቀዱላቸው። አባ እስጢፋኖስ እናአቋማቸውን የሚጋሩ መነኮሳት ጭምር ይኖሩበት የነበረውን ገዳም ለቀው በመውጣትአዲስ ገዳም (ደብረ ገርዜንን) መሠረቱ።

አባ እስጢፋኖስ ተከታዮችን አብዝተው ደብረ ገርዜንን መስርተው ከከሳሾቻቸው ቢርቁም ከሳሾቻቸው ይከታተሏቸው ነበር። እንዲያውም አዲስ ለመጣ ሹም ሁሉ ክሳቸውን እንደ አዲስ ያቀርቡ ነበር። የአባ እስጢፋኖስ ተቃዋሚዎች ከገዳሙ አስተዳደር አልፈው ንጉሥ (አጼይስሀቅ[10]) ዘንድ ከሰሷቸው። በ1421 ዓ.ም ንጉስ አጼ ይስሐቅ ዘንድ አባ እስጢፋኖስና ተከታዮቻቸው በአደባባይ ለተከሰሱበት ክስ ምላሽ እንዲሰጡ ተጠየቁ። ተከሳሹ አባ እስጢፋኖስ እና ከከሳሾቹ መካከል በውክልና ጳጳሱ ባሉበት ንጉሥ ፊት ቀርበው ከሳሽ ክሱን እንዲያቀርብ ተደረገ። ሆኖም

[9]አባ በርተሎሜዎስ
[10]አጼ ይስሀቅ (1412_1430 እ.አ)

ከሳሾቹ ክሳቸውን በትክክል ሳያስረዱ እግረመንገድ በተነሳ የምንኩስና ህይወት (አኗኗር)[ii] ከሳሽና ተከሳሾች ምልልስ አደረጉ። ክሱን በሚያደምጡት ገለልተኛ ወገኖች ዘንድ አባ እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያኗ የምትቀበላቸውን መጻህፍት በአስረጅነት በመጥቀስ በሰጡት ማብራሪያ በተከሰሱበት አደባባይ አዋቂነታቸውን አስመሰከሩ። እንዲያውም ለአባ እስጢፋኖስ ለክስ የቀረቡበት አደባባይ አቋማቸውን ሌሎችም እንዲያውቁት፣ እንዲከተሏቸው የበለጠ መንገድ ከፈተላቸውእውቅናም አሰጣቸው። ሆኖም ክሱ በአጼ ይስሀቅ ዘመን ብቻ ያበቃ አልነበረም።

የአባ እስጢፋኖስና የሀሳባቸው ተጋሪዎችን ከሳሾቻቸው አዲስ ንጉስ ሲነግስ ጠብቀው ክሳቸውን አጠንክረው እንደአዲስ መክሰሱን ቀጠሉበት። ከከሳሾቻቸው መካከል ጥቂቶቹ ሃይማኖቱ ጉዳያቸው ሆኖ ሳይሆን በመነኮሳቱ ሰበብ ንጉሡ ፊት በመቅረብ ሹመት ለማግኘት የሚፈልጉምነበሩበት። ይህን የሚጠቁመው ደግሞ አጼ ይስሀቅ አልፈው አጼ ዘርያእቆብ ሲነግሱበአባ እስጢፋኖስ እና በተከታዮቻቸው ላይየቀረበባቸው ክስ ነው።ክሳቸው የነበረው፤ አንደኛው፣ የሀገራችን ትምህርት ያልሆነ ያስተምራሉ። ሁለተኛው ሥርዓት ይሽራሉ። ሶስተኛው፤ አባቶች ያላስተማሩንን ሌላ ትምህርት ያመጣሉ የሚሉ ናቸው(ደቂቀ እስጢፋኖስ 79፣ 80 እና 87)። እነዚህየክስ ዝርዝሮች አጼ ዘርያእቆብ ከመንገሳቸው በፊትም የነበሩ እና የሚደጋገሙ ናቸው።

በአባ እስጢፋኖስና በተከታዮቻቸው ላይ በአጼ ይስሀቅ ዘመን ከተነሳባቸው ክስ የተለየ ባይሆንም “ግፉበት” አልተባሉም። እንዲያውም የገድሉ ጸሀፊ አባ እስጢፋኖስን “ቅዱስ” አሰኝቶ ገድልያጻፈላቸው ታሪክ ከዚህ በኋላ የተከሰሱበት ክስ እና ላመኑበት እውነት ግንባራቸውን በመስጠት ለገድሉ አንባቢ ጭምር የአባ እስጢፋኖስ ተከታዮች አሰቃቂ መከራ ስለደረሰባቸው ነው።

አባ እስጢፋኖስ በንጉሡ አደባባይ ቀርበው በተደጋጋሚ የሚቀርብላቸው የተለመደ ጥያቄ በመሆኑ የሰጡት ምላሽ፤ “ምንድን ነው ብዙዎች ሁሉ አድርገውታል በማለት የነገር ድካም?” የሚል ነበር። ይህ የአባ እስጢፋኖስ ምላሽ ከከሳሾቹ በበለጠ ፍርድ ሰጪውን ንጉስአጼ ዘርያእቆብን አስቆጣ። የዘመኑ ልማድ የነበረው ለንጉሡ በተለያየ መልኩ አክብሮትን ማሳየት ነው። ንጉሡን ያስቆጣው የአባ እስጢፋኖስ ምላሽ፤ አባቶች ካደረጉት ማድረግ፣ ከተቀበሉት መቀበል፣ አባቶች ከሰገዱ መስገድ በአጠቃላይ የቆየውን ደንብና ስርዓት መሻር አይቻልም የሚለው የንጉሡን አቋም የሚገዳደር መሆኑ ነው። ንጉሡ ደግሞ ይህንን አቋም ካልያዝኩ አባ እስጢፋኖስን ሌሎችም ይከተሏቸው እና የንጉስነት ክብሬ ይቀንሳል የሚል ስጋት እንዳለበት የሚጠቁሙ ፍንጮችን እናገኛለን።

[ii]በአባ እስጢፋኖስ እና በከሳሾቻቸው መነኮሳት መካከል ስለምንኩስና አኗኗር እንደ መመሪያ የሚከተሉትን መጻህፍት በማወቅና በመረዳት ትልቅ ልዩነት አላቸው። ከሳሹ መነኩሴ፣ ዓለምን መተው ንብረት ማፍራት የዓለም ስልጣን መፈለግ መክሰስ፣ መከሰስ መፍረድ ማስፈረድ ይገባኛል ባይ ናቸው። አባ እስጢፋኖስ ደግሞ ይህ ሁሉ ለእኛ አይገባም። እኛ ዓለም ውስጥ ብንኖርም ከዓለም ተለይተናል ሲሉ አባ እስጢፋኖስ መጽሀፍ ቅዱሱን በመጥቀስ ሰፊ ማብራሪያ በማስረጃ በዚሁ መድረክ አቅርበዋል።

ለምሳሌ በዘመኑ ህዝቡ ንግሱ ፊት ብቻ ሳይሆን በሌለበት ስሙ ሲጠራ ይሰግዱ እንደነበረ የሚከተለው ጽሁፍ ይጠቁመናል።

> እነዚህ ሰዎች ሕዝቡን (በተለይም መንግስቱን)የሚከፋፍሉበት መስሎት ትልቅ ስጋት አደረበት፤ ጥያቄያቸውን መመለስን የራሱ ጉዳይ አደረገው። እስጢፋኖሳዊያን ተከሰው ከንጉሡ ችሎት ሲቀርቡ እጅ መንሳት እንደስግደት ቆጥረው ዝም ብለው ከፊቱ ሲቆሙ ጊዜ የባሰውን ይናደድ ነበረ። በዘመኑ ሥርዓት መሠረት ዜጋዎች እንኳን ከንጉሡ ቀርበው በሌለበት ቦታም ስሙ ሲጠራ መሬት ድረስ ለጥ ማለት ነበረባቸው (ጌታቸው፣ 2010፡ 26)።

ንጉሡ አባ እስጢፋኖስ በአደባባይ በሰጡት ምላሽ መቆጣታቸውን በግልጽ ሳይሆንበተለያየ መንገድ ገልጸዋል። ለምሳሌ ንጉስ አጼ ዘርያዕቆብ አባ እስጢፋኖስን እንዲመጡ አዘውአባ እስጢፋኖስና ተከታዮቻቸው ካሉበት ገዳም ተነስተው ረዥም መንገድ ተጉዘው ንጉሡ ደጅ ቢደርሱም፤ እንደመጡ አላናገሯቸውምሆን ብለው ደጅ አስጠንተዋቸዋል። ንጉሡ አባ እስጢፋኖስን ደጅ ማስጠናታቸው ቀድሞም ለክብሬ አልተንበረከካችሁም ብለው እንዳቄሙ ማሳያ ምልክት ነው።

ሁለተኛው ንጉሡን ያስቆጣቸው"ምንድን ነው ብዙዎች ሁሉ አድርገውታል በማለት የነገር ድካም"የሚለው የአባ እስጢፋኖስ ምላሽ ነው (ደቂቀ እስጢፋኖስ 109)። አባ እስጢፋኖስ የመንጋውን እምነት "የነገር ድካም" ብለው ማቅለል ህዝቡ ለንጉሡ ይሰጥ የነበረውን የአክብሮት መግለጫ ልማድ መፈታተን ነው። የአባቶች ስርዓት ላይ ማመጽ ነው። አባ እስጢፋኖስ በንጉሡ አደባባይ ቀርበው በተደጋጋሚ ለሚቀርብላቸው የተለመደ ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ንጉሡን ከከሰሱት መነኮሳት የባሰ አስቆጣው።

አባቶች ካደረጉት ማድረግ፣ ከተቀበሉት መቀበል፣ አባቶች ከሰገዱ መስገድ በአጠቃላይ የመንጋውን ደንብና ስርዓት መሻር አይቻልም የሚለው ደግሞ የንጉሡ አቋም ነው። ይህንን አቋም ካልያዝኩ ሌሎችም ይከተሏቸው እና የእኔ ክብር ይቀራል የሚል ስጋት ያለበት ይመስላል። ስጋቱም በተግባር አንድ አበምኔት ለቅዱሱ.... ደብሬን ተረከበኝ /ውሰድ እኔንም ስለ እግዚአብሄር ብለህ አንተ ቅበረኝ፣ በአንተ ሥርአት ስር እንድሆን እፈልጋለሁ....ነፍስና ስጋን በመርዳት ለሀገራችን ትልቅ መከታ ተገኘ (ደቂቀ እስጢፋኖስ 97፣ 106)። ይህ በገድል ውስጥ የምናገኘው ሀሳብ የሚጠቁመው የአባ እስጢፋኖስ ሀሳብ ተጋሪዎች መበርከት ነው። የንጉሡም ስጋት የነበረው የአባ እስጢፋኖስ ሳይሆን የተከታዮቻቸው እየበረከቱ መምጣት ነው።

ሶስተኛው እና የበለጠውን በንጉሡ እና በአባ እስጢፋኖስ መካከል ወደ ከረረ ግጭት ያሸጋገራቸውለአብ ለወልድ እና ለመንፈስ ቅዱስ እንጂ ለሌላ ስግደት አይገባም (ደቂቀ እስጢፋኖስ 30፣ 105፣ 123) የሚለው የአባ እስጢፋኖስ እና የተከታዮቻቸውን አቋም በንጉሡ ፊት መግለጻቸው ነው። ንጉሡም ፊት ለፊት "አትሰግድልኝም፣ አንቱ አትለኝም" (ደቂቀ እስጢፋኖስ 102፣ 109-110)። የሚለው ደግሞ በዘመኑ የተለመደውን ልማድ የሚንድ በመሆኑ ነው።

ደቂቀ እስጢፋኖሳዊያንም ንጉስ ዘርያእቆብ እኛ የምንከተለው አቋም ሳያውቀው ቀርቶ ሳይሆን ልማዱ እንዲቀር ስለማይፈልግ ነው ሲሉ በገድል ውስጥ ጠቁመዋል። ይሄውም፣ "የሚጠላን ስለአባቶቹ ስርዓት እንጂ ስለ እግዚአብሄር ህግ አይደለም" (ደቂቀ እስጢፋኖስ 106)። አባ እስጢፋኖስና ተከታዮቻቸው ደግሞ ንጉሥ ስለተቆጣ የሚፈሩ ወይም ያመኑበትን በድብቅ የሚያደርጉ አልነበሩም። "ትክክል ነን" ብለው ላመኑበት አቋማቸው የጸኑ ነበሩ። ጽናታቸውም ለመነኩሴ በስርዓቱ እንዳለ ከመሞት የሚሻለው የለም የሚል ነበረ።

### 3.2 ለመነኩሤ በስርዓቱ እንዳለ ከመሞት የሚሻለው የለም፤...ሥርዓት ለሚሞትላት ነች[12]

"የመነኩሴ ግዴታው አይኑን ጨፍኖ በእምነት መታገል ነው።"የሚል አቋም ያላቸው አባ እስጢፋኖስና ተከታዮቻቸው መከራውን ሁሉ የተቀበሉት ስለገቡበት የምንኩስና ህይወት ብለው እንደሆነ ይገልጻሉ። በመነኮሳት ላይ ፈተና ያለ ቢሆንም በተለይ "....እውቀት ባላቸው በረጅሙ በሚያስቡ የጽድቅ ስርዓት ትጠነክርባቸዋለች (ደቂቀ እስጢፋኖስ 263)" በማለት በገድሉ ውስጥ አቋማቸው ተጠቁሟል።

አባ እስጢፋኖስ ይኖሩበት ከነበረው ገዳም አበ ምኔት ጀምሮ ሁለቱ ነገሥታት ድረስ የተከሰሱበት ክስ በአባ አበክረዙንና በሌሎቹ ደቂቀ እስጢፋኖሳዊያን ከቀድሞው በጠነከረ መልኩ ቀጥሏል።

አጼ ዘርያእቆብ ደግሞ ንጉስነውና ንጉስ በግዛቱ ያሉ ህዝቦች ላይ እንደሀሳቡ ካልኖሩ የፈለገውን ማድረግ ይችላል፤ የአጼ ዘርያእቆብ አቋምም ይሄው ነበር። ከዚህ በኋላ በደቂቀ እስጢፋኖሳዊያን ላይ የተለያየ መከራ ደርሶባቸዋል። ለምሳሌ፡-መግረፍ፣ በምላጭ መብጣት፣ በምላጭ መከተብ (የንጉሡ ባሮች ናችሁ የሚለውን ለማሳየት)፣ ማሰር፣ መግረፍ፣ ልብሳቸውን መግፈፍ፣ በአጠቃላይ የተለያየአይነት አካላዊ እና ስነልቦናዊ ቅጣት ተቀጥተዋል። በቅጣቱ መብዛት አባ እስጢፋኖስን ጨምሮ የሞቱት በርካታ ናቸው።

አባ እስጢፋኖስ መከራው ለሞት አበቃቸው። አባ እስጢፋኖስ ከዚህ አለም በሞት ሲለዩ ተከታዮቻቸውን ለማጥፋት የአባ እስጢፋኖስ አጽማቸው ከሶስት ጊዜ በላይ እንዲፈልስ በመጨረሻም እንዲቃጠል ተደርጓል። የአባ እስጢፋኖስ  አጽም የተቃጠለበት ቦታ ብረሃን ታየ የአባ እስጢፋኖስ ተከታዮች የታየውን ብረሃን "ተአምር ታየ" ሲሉ ተርጉመውታል። ተአምሩም ለአባ እስጢፋኖስ ተከታዮች እና ለንጉስ ዘርያእቆብ (ለደቂቀ እስጢፋኖስ ተቃዋሚዎች) ብረሃን መታየቱ ተአምር ስለመሆኑ ተመሳሳይ ትርጉም ቢሰጡትም አንድምታው የተለያየ ነበር። የአባ እስጢፋኖስ አጽም ሲቃጠል ብረሃን መታየቱ፤ ለንጉስ ዘርያእቆብ እና ለደጋፊዎቻቸው የአባ እስጢፋኖስን አጽም ማቃጠላችን እንዲሁም "ደቂቀ እስጢፋኖሳዊያን ላይ የወሰዱት ቅጣት ተገቢ መሆኑን ፈጣሪ በተአምር ያረጋገጠበት ነው።" የሚል ትርጉም በመስጠት ብርሃን የታየበትን ቦታ ንጉስ ዘርያእቆብ የቀድሞ ስሙ ቀርቶ ደብረ ብረሃን እንዲባል ወሰነ። እስካሁን ደብረ ብረሃን የሚለው የአጼ ዘርያእቆብ የሰጠው ስያሜ የአካባቢው መጠሪያ ሆኖ ያገለግላል። ደቂቀ

---

[12] (ደቂቀ እስጢፋኖስ 267)

እስጢፋኖሳዊያን ደግሞ ብረሃን የመታየቱ ወይም የተአምሩ ፍቺ "የአባ እስጢፋኖስ አጽም ፈልሶ በመቃጠሉ ፈጣሪ በቁጣ የላከው ብረሃን ነው" የሚል ነበረ።

አባ እስጢፋኖስ ቢያልፉም አጼ ዘርያእቆብ እረፍት አላገኙም። ምክንያቱም አባ እስጢፋኖስ ብዙ መሰል አቋም ያላቸውን መነኮሳት አፍርተው ነበር። "የትምህርቱ ስብከት እንደዚህ መሠረት ያዙች እኮ (ደቂቀ እስጢፋኖስ 113)" ሲልንጉሡ መናገሩን በዚሁ ገድል ውስጥ ጠቁመውናል። እንዲያውም የአጼ ዘርያእቆብ ልጅ[13] ጭምር ከደቂቀ እስጢፋኖሳዊያን ወገን ነበር።ደቂቀ እስጢፋኖሳዊያን የእነሱን መጠንከር የንጉሡንም ደቂቀ እስጢፋኖሳዊያን ላይ መጨከን ሲገልጹ "ጽኑ ነብይ ሲነሳ ጽኑ ንጉስ ያስነሳል" በማለት ነው።

### 3.3 ጽኑ ነቢይ ሲነሳ እንደዚሁ ጽኑ ንጉስ ያስነሳል[14]

አባ አበክረዙን የአባ እስጢፋኖስን ፈለግ በማስቀጠል በእድሜም ከአባ እስጢፋኖስ በላይ የኖሩ እና በየሀገሩ በድብቅ እየዞሩ ተከታዮቻቸውን እንዲበዙ እና በመከራ እንዲጸኑ በማድረግ ይታወቃሉ። "ትክክሉ የመንፈስ አባቱን ነገር መጠበቅ የቃሉን ምስክርነት ልብ ማለት (ባባቱ) ቁመት ልክ ለመቆም እስኪደርስና ከፍ እስኪል ድረስ የፈለጉን መአዛ መከተል ነው (ደቂቀ እስጢፋኖስ 258)።" የሚል አቋም ነበራቸው።

ስግደት በአፄ ዘርያዕቆብ እና በአባ እስጢፋኖስ እንዲሁምበተከታዮቻቸው መካከል ለተነሳው አለመግባባት ዋነኛው ምክንያት ሆኖ በአደባባይ በተለይም ለአብዛኛው ህዝብ ይገለጽ ነበር። በተለይ "ለሌላ አንሰግድም" የሚለው ትምህርት መሠረት ከያዘ ለንጉሡ የማይንበረከክ የሰዎች ቁጥር መብዛቱ የንጉሡ ዋንኛ ስጋት ነበር። ይህንንም በንጉሡ ዘንድ ለንጉሡ አሳቢ መስለው ሹመትና መወደድን ከንጉሡ ለማግኘት "እነዚህን እንደዚህ ዝም ካልካቸው ሁሉም የነሱን ፈለግ ይከተሉና ለመንግስትህ ስልጣን የሚሰግድ አይኖርም (ደቂቀ እስጢፋኖስ 2006፡ 105)" በሚል ግጭቱን የሚያከሩ ነበሩ።

ስለዚህ የንጉሡ አማራጭ የነበረው እስጢፋኖስን "እስጢፉ" ተከታዮቹን እስጢፋዊያን ብሎ ማግለል አግልሎም ከቤተ መንግስቱ እና ከቤተክህነቱ ማባረር ነው። ለዚህም የህዝቡን ቀልብ መሳቢያ "ከእግዚአብሄር ሌላ የሚለውን ማፍረሻ ውግዘትና ቅጣት ማጽደቂያ ጠቡን ግላዊ ከማድረግ ከማሪያም ጋር ማድረግ ጠቡ ተቋማዊ ስለሚሆን ለቤተመንግስቱ ወገን ፋይዳው ከፍተኛ ነው። በዚህም ምክንያት "ለማርያም የማይሰግዱ" የሚለው የደቂቀ እስጢፋኖሳዊያን መታወቂያ እንዲሆን ከፍተኛ ዘመቻ ተደርጓል።

መነኮሳቱን ያን ያህል መከራ እንዲቀበሉ ያደረጋቸው እና በመከራ ያጸናቸው እውን የማሪያም ጉዳይ ብቻ ነው ወይ? ስንል አይደለም ለማለት የሚያስችል ማስረጃዎች እናገኛለን። ለምሳሌ፡- ለማሪያም ስገዱ ቢሏቸው፤ …ማሪያምን ለልጇ ስንሰግድ እዚያ እናገኛታለን። "…ለአምላክ እናት

---

[13]የአጼ ዘርያእቆብ ወንድ ልጅ አባ እስጢፋኖስ መጀመሪያ ከነበሩበት ገዳም ጀምሮ ከጎናቸው የነበሩት የአባ አበክረዙን ተማሪ ነበረ (ደቂቀ እስጢፋኖስ 254)።

[14]ደቂቀ እስጢፋኖስ (254)

ለማሪያም ስግደት ብንሰግድ አያሳዝነንም፡፡ለማሪያም ሰገዱ..ለማሪያምና ለሰላም መስቀል እንሰግዳለን አሉ፡፡ እንዲሁም "የአምላክ እናት ሆይ እነሆ ከማህጸንሽ ጥላ ስር ተደምረናል፡፡ በጭንቃችን ጊዜ ልመናችንን አትናቂ (ደቂቀ እስጢፋኖስ 140፣ 146፣148፣ 149)፡፡" በማለት መነኮሳቱ ስለማሪያም ያላቸውን አቋም የሚያሳዩ መረጃዎችን ከገድላቸው ውስጥ እናገኛለን፡፡

ደቂቀ እስጢፋኖሳዊያን ላይ ንጉሡ እና ባለሟሎቹ የተለያየ መከራ አድርሰውባቸዋል፡፡ ከቅጣትም በላይ ህዝቡ እንዲያገላቸው አዋጅ ታወጀባቸው፡፡ አዋጁ ለምሳሌ "እስጢፋኖስ እርኩስ ነውበለው'አዎን፣ እርኩስ ነው' ሲልህ፣ ሰላም በለው በእንግድነትም ሲመጣ በእህልም በውሃም ተቀበለው፡፡ አለዚያ ከእስጢፋኖስ ልጆች አንዱ እንደሆነ እወቅ[5]" የሚል ነበረ፡፡ በአጠቃላይ ደቂቀ እስጢፋኖሳዊያን ይከሰሳሉ፣ ይንገላታሉ፣ ይዘረፋሉ፣ ይደበደባሉ፣ ይገደላሉ፡፡ ሆኖም አዋጁን ከሚተገብረው ህዝብ መካከል የደቂቀ እስጢፋኖሳዊያን ሀሳብ የሚደግፉ እና ፊት ለፊት መጋፈጥ የማይፈልጉ በርካታ በመሆናቸው ለደቂቀ እስጢፋኖሳዊያን ከለላ ይሰጧቸው ነበር፡፡

ደቂቀ እስጢፋኖሳዊያን "ትክክል ነው" ብለው ለአመኑበት እውነት እስከሞት የጸኑ ነበሩ፡፡ ከሳሽ መነኮሳት እና በተለይ ንጉሡ እኔ ያልኩት ካልሆነ በስተቀር የትኛውንም በኀይል፣ በገንዘብ፣ በስልጣን ማድረግ የሚችሉትን ሁሉ ከማድረግ ወደ ኋላ አላሉም፡፡ የኀይሉን መመጣጠን ተከሳሽ መነኮሳቱ ተረድተው ይመስላል ስለራሳቸው እና ስለከሳሾቻቸው "ጽኑ ነቢይ ሲነሳ እንደዚሁ ጽኑ ንጉስ ያስነሳል" ብለው የተናገሩት፤ የሆነውም ይሄው ነው፡፡

## 4. መደምደሚያ

በአጠቃላይ ደቂቀ እስጢፋኖሳዊያኑ (ተከሳሹ ወገን) ከጅማሬ እስከ ፍጻሜው የሃይማኖት ጽንሰ ሀሳብን ከተጻፉ የህግ መጻህፍት ማስረጃ በመጥቀስ የምንኩስና ህይወት በመመሪያው መሰረት መሆን አለበት የሚሉ ናቸው፡፡ ሲከሰሱ የሚያቀርቡት ማስረጃ ከሳሽ መነኮሳቱ እንዲሁም ፈራጅ የሆኑት ሀገረ ገዢዎችና ንጉሡ ጭምር የሚከተሉት ሃይማኖት የተቀበሏቸው መጻህፍት ናቸው፡፡ መጽሀፍቱን የተረዱበትን አንድምታ በማንኛውም ሁኔታና እንደጠያቂው ወይም እንደከሳሹ ማህበራዊ ዳራ የሚቀየር የሚለዝብ ወይም በፍርሀት የሚሻሻል ወይም ማስመሰል ያለበት ሳይሆን የማይቀየር አቋም የሚያመለክት ነው፡፡

ገድሉ ዐውደ ንባቡ የሃይማኖት ነው፡፡ በአውደ ንባቡ ውስጥ ያሉት ድርጊቶች ሁነቶች እና ሁኔታዎች ሃይማኖታዊ ናቸው፡፡ በእምነት ዓይን አይተን በእምነት ጆሮ ሰምተን በእምነት ልቡና አምነን ይሁን ብለን የምናስተናግዳቸው ናቸው፡፡ አንድ ገድል የሚጻፍለት ግለሰብ ባለ ገድል ለመሆን ይዞ የሚነሳው አላማና ለስኬቱ ሲል የሚያልፍባቸው አባጣ ጎባጣ መንገዶች አሉ፡፡ አላማው ፖለቲካ፣ ሃይማኖት ወይም ሰብአዊነት ሊሆን ይችላል፡፡ ቅዱስ ያስባለው ገድል የተጻፈለት ለሚከተለው ሃይማኖት ከእርሱ የቀደሙ የሃይማኖቱ ተከታዮች በደነገጉትና በጽሁፍ ላሰፈሩት ቀኖና ታማኝ መሆን ነው፡፡ ምድራዊው ተጋድሎ ከሞት በኋላ አለ ለሚለው ዓለም

[15]በንጉሡ አዋጅ ደቂቀ እስጢፋኖስ እንኳን ከቤተክርስቲያን ከቤተ ምእመናንም እንዳይገቡ ክልክል ነው (136)፡፡

ለመብቃት የተደረገ ትግል ነው። ትግሉን ማሸነፍም ከሞት በኋላ ባለው ዓለም በተድላ ዘላለማዊ መሆን ነው።

በአጼ ይስሀቅ ዘመን ደቂቀ እስጢፋኖሳዊያን ትምህርታቸው ትክክል መሆኑን በመመስከር በትምህርቱም ግፉበት ይሏቸዋል። እንደገና በአጼ ዘርያእቆብ ዘመን የነበሩ ጳጳስ ዘንድ ለክስ ይቀርባሉ። ግን የሃይማኖት ህጸጽ አለባቸው ሳይሉ ተድበስብሶ ያልፋል። በቤተክርስቲያኗ በተቀባ ንጉስ የሃይማኖት ህጸጻቸው በግልጽ ሳይነገር እጅግ አሰቃቂ መከራ ይደርስባቸዋል።

የከሳሾቹ ጥያቄ በሰበካው የሃይማኖት ነው። ውስጡ ግን ተበለጥኩ ወይም ስልጣኔን ልቀማ እችላለሁ የሚል ፍራቻ ነው። አንዳንዴም ሙሉ በሙሉ ሽፋን የሆነው የሃይማኖት ጥያቄ ይረሳና የንጉስነት ክብር ለጥያቄ ይቀርባል። አንዱ ወገን ወይም ተከሳሹ ከጅማሬ እስከ ፍጻሜ የሃይማኖት ጽንሰ ሀሳብን ከተጻፉ የህግ መጻህፍት ማስረጃ የሚያቀርብ መጽሀፍቱን የተረዳበትን አንድምታ በማንኛውም መንገድ የማይቀየር አቋም ያለው ነው። ይኼውም ለሚቀርብባቸው ክስ ሀሳብን በሀሳብ ወይም እምነትን በተጻፉ መጽሀፍት ማስረጃነት መርታት ነው። ሆኖም ከሳሾቹ "ሃይማኖት" የጥያቄው ሽፋን ይሆንና ዋናው ጥያቄ ስልጣን መሻት፣ የነበረን ስልጣን ላለማጣትም ነው። ስለዚህ የከሳሾቹ አቋም እምነትን ወይም ሀሳብን በማስረጃ ለመርታት መሞከር አልሆን ሲል በስልጣን ወይም በሀይል መርታት ነበር።

በኋላም ፍርድ ሰጪው ንጉስ ፍርድ መስጠቱ ቀርቶ ዋና ከሳሽ እና አሳዳጅ ሆኖ ከሳሾቹ ከንጉሡ ኋላ ተከታይ ይሆናሉ። የከሳሾቹ ጥያቄ የሃይማኖት ሽፋን እንደሆነው ሁሉ ንጉሡም በእነሱ መንገድ ገብቶ ኋላ ላይ በግልጽ "በንጉስነቴ አልተሰገደልኝም" እንዲሁም "አንቱ አልተባልኩም" የሚለው ክስ ተከሳሾቹንና ተከታዮቻቸውን ለመከራ ዳርጎ በተከታዮቻቸው ዘንድ ገድል እንዲጻፍላቸው አድርጓል። ይህ ገድል ንጉሡ አባ እስጢፋኖስንና ተከታዮቻቸውን ለፈጣሪ እንደምትንበረከኩት ሁሉ ለእኔም ለምድራዊው ንጉስ ለክብሬ ተንበርከኩ ከሚል አንድምታ የመነጨ ነው።

የደቂቀ እስጢፋኖስን ገድል ከሌሎች ገድሎች ልዩ የሚያደርጉት ሁለት ጉዳዮች ናቸው። አንደኛ ገድሉ በተሳታፊ ተመልካች መጻፉ ነው። ሁለተኛው የገድሉ ይዘት ነው። የደቂቀ እስጢፋኖስ ገድል (ታሪክ) ከተለመደው የገድል ይዘት ይለያል። አብዛኛዎቹ ገድሎች ይዘታቸው ተጋድሏቸው ከአጋንንት አልያም ከሌላ ሃይማኖት ተከታይ ነው። የአባ እስጢፋኖስ እና የተከታዮቻቸው ተጋድሎ ግን በአንድ ገዳም ከሚኖሩ ጓደኞቻቸው መነኮሳት ይጀምራል። ክሱ ጳጳሳት ዘንድ ይቀርባል። ጳጳሱም ሆኑ ንጉሡ እና ባለሚሎቹ በአንድ ሃይማኖት ተቋም የሚተዳደሩ ናቸው። አሳዳጅ እና ተሰዳጅ ወይም ከሳሽ እና ተከሳሽ የሆኑት ሁለቱም በአንድ የሃይማኖት ተቋም ስም የሚተዳደሩ እና ስለ እምነቱ ይገደናል የሚሉ መነኮሳት ናቸው።

የአባ እስጢፋኖስ ተከታዮች ለአመኑበት እውነት መሞትን የማይፈሩ ነበሩ። አቋማቸው ከግለሰብ ወደ ተቋም አሸጋግረውታል። ተቋሙም ደቂቀ እስጢፋኖስ ለመባል በቅቷል። በደቂቀ እስጢፋኖስ መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱ ሶስት ገድሎች የተቋሙ ውጤት ናቸው።

## ዋቢ ጽሁፎች

በአማን ነጸረ። 2009። *ወልታ ጽድቅ።* ፋር ኢስት ትሬዲንግ።

ብርሃኑ ገበየሁ። 1999። *የአማርኛ ሥነግጥም።* አዲስ አበባ። ንግድማተሚያ ቤት።

ገድለ አቡነ እስጢፋኖስ ዘጉንዳጉንዶ። 1996። *ዘአጠም መምህር ወማህበር ዘጉንዳጉንዶ ደብረ ገሪዛን ማሪያም ገዳም*።

ጌታቸው ሀይሌ (ተርጓሚ)። *ደቂቀ እስጢፋኖ(በህግ አምላክ)*። ሁለተኛ እትም። 2006። አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ፕሬስ።

ዳንኤል ክብረት። 2011። *ኢትዮጵያዊው ሰራፊ የአቡነ ተክለሃይማኖት የሕይወት ታሪክና አስተዋጽዖ*። ፋር ኢስት አታሚዎች።

ኪዳነወልድ ክፍሌ። 1948። *መፅሐፈ፡ ሰዋሰው፡ ወግስ፡ መመዝገበ ቃላት ሐዲሱ*። አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

Crawford, VM. 1961. *The Legends of the Saints: An Introduction to Hagiography*: Translation from French.

Getachew Haile. 1983. "The Cause of the Estifanosites: A Fundamentalist Section the Church of Ethiopia." In *Religion*: Misce11anea: AAU.